# በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

## የተሽከርካሪዎች የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች መወሰኛ እና የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ማብራሪያ

መጋቢት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## 1. <u>መግቢያ</u>

እንቅስቃሴ ለሰዉ ልጅ የተፈጥሮ ህግ ከመሆኑም በላይ ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት በሀገራችን ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ እድገት እንዲሁም ለወጪና ለገቢ ንግድ መስፋፋትም ሆነ መጨመር ከፍተኛዉን ድርሻ የያዘዉ የመንገድ ትራንስፖርት እንደሆነ ግልጽ ነው:: በሀገሪቱ 90 ፐርሰንት ጭነት እንዲሁም 95 ፐርሰንት ህዝብ ከቦታ ወደቦታ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ተደራሽ የሚደረገው በመንገድ ትራንስፖርት አማካኝነት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የመንገድ ትራንስፖርት የአንድ ሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መለኪያ ብቻ ሣይሆን የሀገሮች የወደፊት የዕድገት ተስፋቸው አመላካች እየሆነ መጥቷል፡፡ ዘመናዊና የተቀናጀ የመንገድ ትራንስፖርት የሚጠቀሙ ሀገሮች በዓለም ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እና የምርቶቻቸው ተወዳዳሪነት እንዲሁም በሌሎች ሀገሮች ላይ ያላቸውን ተፅእኖ ፈጣሪነት በእጅጉ ከሚወስኑ ጉዳዮች አንዱ ሆኗል፡፡ ይህ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት በዋናነት የሚካሄደው በባለሞተር ተሽከርካሪዎች ሲሆን የባለሞተር ተሽከርካሪዎች በመጠንም ሆነ በአይነት ከመጨመር ጋር ተያይዞ በመንገድ ላይ የሚሽከረከሩትን ተሽከርካሪዎች መዝግቦ መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከ1934ዓ.ም ጀምሮ ህግና ደንብ ወጥቶለት ከ80ዓመታት በላይ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡

በ1994 ዓ.ም አዲስ የተሽከርካሪ ሠሌዳ ለዉጥ ከተደረገ ወዲህ **እስከ 2015 ዓ.ም በሀገሪቱ 2,214,594 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ ህ አምስት መቶ ዘጠና አራት**/ሰሌዳዎች ተመርተው ተሰራጭተዋል፡፡ ያለን የተሽከርካሪ ብዛት ከሌሎች ሀገራት አንጻር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም የትራንስፖርት ዘርፉ ከፍተኛ ቁጥር ላለዉ የህብረተሰብ ክፍል የስራ እድል እየፈጠረ ስለሆነ ባለሃብቱ በትራንስፖርት ኢንቨስትመንት ያለዉ ተሳትፎ እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በአሁን ጊዜ የአንድን ሀገር እድገት ከሚያመላክቱ ዓበይት ጉዳዮች መካከል የትራንስፖርት አገልግሎቱ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። የየብስ ትራንስፖርት በዋናነት በተሽከርካሪ የሚካሄድ ሲሆን ተሽከርካሪን ለመመዝገብ፣ ለመቆጣጠር፣ የአገልግሎት ዓይነትን እንዲሁም መዝጋቢዉን አካል ለመለየት

እና ስምሪት ለመስጠት የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ወሳኝ የመረጃ ምንጭ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡

ይሁንና በቀድሞው የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሰረት ሲሰጡ የነበሩ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሰሌዳ አይነትና ምልክቶች፣ አመራረት፣ አሰረጫጨትና አወጋገድ ወቅቱ ከሚጠይቀዉ ተጨባጭ ሁኔታና የአገልግሎት አሰጣጡ ከዘርፉ ዕድገት ጋር ባለመጣጣሙ፤ እንዲሁም ሀገራችን ተቀብላ ካጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አኳያ ዓላማው አሁን ከተደረሰበት እና ወደፊት ከሚደርስበት የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎትና ዕድገት አንጻር አብሮ የሚሄድ ባለመሆኑ እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጡ ምልልስ የበዛበት፣ ሀብትንና ጊዜን የሚያባክን፣ ተገልጋዩን ያላረካ፣ ለሙስናና መልካም አስተዳደር ችግሮች የተጋለጠ፣ የማምረትና የማሰራጨት ሂደቱ የተንዛዛ፣ ትራንስፖርት ቢሮዎችን ለከፍተኛ ወጪ የዳረገ በመሆኑ ያለውን ውስን የሀገር ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የተሽከርካሪዎችን ሰሌዳ መለያ ቁጥር አይነትና ምልክቶችን ሀገራችን የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ የመለያ ቁጥር ዓይነትና ምልክቶችን፣ የሠሌዳ አመራረትን፣ ስርጭትና አወጋገድ ላይ የሚታዩትን ችግሮች በመቅረፍ በጥናት ላይ የተመሰረተ ወጥ የሆነ አሰራር ለመፍጠር ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 2. <u>ለመመሪያው መዘጋጀት አነሳሽ ምክንያቶች</u>

- ቀደም ሲል የነበረው የሠሌዳ አመራረት እና አሰረጫጨት አሠራር ክፍተት የነበረበት እና የሀብት ብክነት ሲስተዋልበት የቆየ በመሆኑ ይህን ሀብት ብክነት በማስቀረት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚመጣውን የሠሌዳ ጥሬ ዕቃ በአግባቡ በመጠቀም የመንግሥትን ሀብት ከብክነት ለመታደግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤
- በተለያዩ ምንያቶች ተመላሽ የሚደረግ የሠሌዳ አወጋገድን በተመለከተ ካሁን በፊት የተዘረጋ ሥርዓት ያልነበረ በመሆኑ የሕግ ማዕቀፍ ኖሮት በሥርዓት እንዲመራ ማድረግ በማስፈለጉ፤
- ካሁን በፊት የነበረው የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አመራረት፣ አሰረጫጨት እና የሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ቁጥር መረጃ አያያዝ ሥርዓት በቴክኖሎጂ የታገዘ ካለመሆኑም ባሻገር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሽከርካሪዎችን ቁጥር በእርግጠኝነት ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኖ በመቆየቱ፤

- የተባበሩት መንግሥታት የመንገድ ትራፊክ ኮንቬንሽን በኦስትሪያ/ቪዬና/ ከተማ እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 7 እስከ ኖቬምበር 8 ቀን 1968 ድረስ በተደረገው ውይይት በተሳታፊ አባል ሀገራት የጋራ ውሳኔ ጸድቆ በሥራ ላይ የዋለ መሆኑን ተከትሎ ኢትዮጵያ ሀገራችንም የተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገር እንደ መሆኗ በኮንቬንሽኑ የተሰጣትን ዓለም-አቀፍ የተሽከርካሪ ምልክት /ETH/ በአግባቡ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲያስችላት ኮንቬንሽኑን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካይነት የተባበሩት መንግሥታት የመንገድ ትራፊክ ስምምነትን ለማጽደቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1260/2013 መሠረት ያጸደቀች በመሆኑና የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርም አግባብነት ካላቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር፣ መንግሥታዊ ከሆኑ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ኮንቬንሽኑን በሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን በአዋጁ የተሰጠው በመሆኑ፤
- በሀገራችን በአሁኑ ወቅት ያለውን የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ምርት፣ ስርጭት እና አወጋገድ አገልግሎት አሰጣጥን ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መንገድ በኢትዮጵያ ለመተግበር፣ መሠረታዊ ለውጥ በማድረግና በሀገሪቱ እስካሁን የተመዘገቡና ወደ ፊት የሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች የሚለጥፉትን የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ወጥ ማድረግና በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ ሀገራዊ ፋይዳው የጎላ በመሆኑ፤

  የሚሉት መመሪያውን ለማውጣት ዋና ዋና አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 3. <u>የመመሪያው መውጣት አስፈላጊነት</u>

- ❖ ቀደም ሲል የነበረውን የዕለት እና ተላላፊ ሠሌዳን አሰጣጥ እና የሠሌዳን ድግግሞሽ በማስቀረት ለዚህ ይውል የነበረውን የግብዓት ብክነት ለማስቀረት፤
- ❖ ካሁን በፊት የዕለት እና የተላላፊ ሠሌዳን እንደ ሽፋን በመጠቀም ለበርካታ ወንጀሎች መፈጸም ምክንያት የሆነውን አሠራር ለማስቀረት፤
- ❖ እስካሁን የነበረው አሠራር ለዕለት፣ ለተላላፊ፣ እንዲሁም ለቋሚ ሠሌዳ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ወደ አንድ በማምጣት በዚህ ምክንያት ይባክን የነበረውን ጊዜ፣ ወጪ እና የሰው ጉልበት…ወዘተ ለመቀነስ፤

- ቀልጣፋና ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥን ለመፍጠር፤
- የተሽከርካሪ ምዝገባ ሥርዓቱን በማዘመን አገልግሎት አሰጣጡ የሚያድግበትን አቅጣጫ ለማስቀመጥ፤
- የተሽከርካሪ ምዝገባ ሥርዓቱንና የትራፊክ ቁጥጥሩን ለማጠናከር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ለመፍጠር፤
- የሀብት አጠቃቀምን ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለማስቀረት፡፡
- ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት ያደረገ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነትና ምልክቶች አጠቃቀምን በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ አሠሰራር ለመፍጠር ነው፤

## 4. ዓላማ

በሀገራችን የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ዉጤታማ ለማድረግ፣ የተገልጋዩን ዕርካታ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ የሰሌዳ መለያ ቁጥር አይነትና ምልክቶች አወሳሰን፣ የተሸከርካሪ ሠሌዳ አመራረት፣ ስርጭት እና አወጋገድ የአሰራር ስርዓት ለመፍጠር እንዲቻል አሁን ያለዉን ሀገራዊ ችግር  በመለየትና የመፍትሔ ሀሳቦችን  በጥናት ለይቶ ለማቅረብ ነው፡፡

## 5. ረቂቅ መመሪያውን ለማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶች

በረቂቅ መመሪያው ላይ ውይይት ሲደረግ ከባለድርሻ አካላት በርካታ ግብዓቶች የተገኙ ከመሆኑም ባሻገር ገንቢ እና ሀገራዊ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ጭምር ከባለድርሻ አካላት አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የመመሪያው መውጣት ተግባራዊ መሆን ወደ ፊት ሀገራዊ አንድነትን ከማምጣት ባለፈ በሀገራችን የሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ከቀጠናው ሀገራት ጋር የሞኖረውን ትስስር ጭምር የሚያጎለብትና ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት የሦስትዮሽ የትራነንስፖርትና የትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራምን ለማሳለጥ ጭምር ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውም ከውይይቱ ተሳታፊዎች ተመላክቷል፡፡

## <u>ሠንጠረዥ 1፡-ከባለድርሻ አካላት የተሰጡ አስተያየቶች</u>

| ተ.ቁ | ከባለድርሻ አካላት የተነሡ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች | ተቀባይነት ያገኙ ሐሳቦች ከነምክንያቶቻቸቸው | ተቀባይት ያላገኙ ሐሳቦች ከነምክንያቶቻቸው |
|---|---|---|---|
| 1 | <u>ከደቡብ፡</u>- ተሽከርካሪ ገና ከውጭ ሲገባ ሠሌዳ እንዲለጥፍ ቢደረግ | ተቀባይነት ያለው ሐሳብ ነው፤ ምክንያቱም የመመሪያው አንዱ ዓላማ ከውጭ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከወደብ ከመግባታቸው በፊት ሠሌዳ አሰይመው እንዲወስጉ ማድረግ ነው፡፡ | |
| 2 | <u>ከሐረሪ፡</u>- የመለያ ቁጥር ሠሌዳ በጥቁር እንዲሆን መደረጉ በቀላሉ የመበላሸትና ፌድ የማድረግ ዕድል አይኖረውም ወይ?<br>- *መመሪያው መዘግየት የለበትም፤ ምክንያቱም በርካታ የተበለሻሹ ነገሮች ስላሉ ብዙ ችግሮችን ይፈታልናል ብዬ ስለማስብ ነው* | ተቀባይነት ያለው ሐሳብ ነው፤ ምክንያቱም ጥቁር ቀለም በዓለም ገበያ ርካሽ በመሆኑና ሌሎቹ ውድ ስለሆኑ የውጭ ምንዛሪን ከመቀነስ አኳያ ከፈፍተኛ ጠቀሜታ አለው | |
| 3 | <u>ከደቡብ ምዕራብ</u>፡- መመሪያው ለእኛ ትልቅ ትርጉም አለው፤ ምክንያቱም ዓለም አቀፍ ስምምነትን መሠረት ያደረገ መሆኑ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሀገር | ደጋፊና ተቀባይነት ያለው ሐሳብ ነው፤ ምክንያቱም ዓለም-አቀፍ ስምምነትን መሠረት ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ወንጀልን በመከላከል | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ደኅንነት ጭምር ትልቅ ፋይዳ አለው | ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው | |
| 4 | **ከአማራ፡-**ቀን ቀን 4 ቁጥር ለጥፎ ሲሠራ ይውላል፤ማታ ማታ ደግሞ ኮድ 3 ለጥፎ ሲነግድ፤ ወርቅ፣ የጦር መሣሪያ ሲጭን ይውላል፤ ይህ አጋጣሚ ማሠልጠኛ ተቋማትም ጭምር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን የምንፈትሽበት አጋጣሚም ነው | ተቀባይነት ያለው ነው፤ አንድ ተሽከርካሪ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሊኖረው የሚችለው አንድ ብቻ እንዲሆን ማስቻሉ 2 እና 3 ሠሌዳ አይኖረውም | |
| 5 | **ከኦሮሚያ፡-** ከሠሌዳ ጋር ተያይዞ አማራጮች ታይተዋል ወይ?<br>- እነዚህ ሠሌዳዎች ሲወገዱ ማነው ወጪውን የሚሸፍነው? 7 ሺ ገደማ ሠሌዳዎች አሉን<br>- በአውቶማቲክ ወይም በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሠሌዳ አሰጣጥን የሚል የለም፤ ከዚህ አኳያ ታሳቢ ቢደረግ፤ | የመጀመሪያው ጥያቄ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ታይተው የሕግ ማዕቀፉ ስለመዘጋጀቱ ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቷል | የመጨረሻዎቹ 2 ሐሳቦች ተቀባይነት አላገኙም፤ አማራ ሠሌዳ ሲወገድ ወጭውን የመዘገበው አካል ነው፤ በስቲከር የሚለይ በመሆኑ፤ በሠሌዳ ልዩነት መፍጠር አያስፈልግም፤ |
| 6 | - የቆዩ ተሽከርካሪዎች በዚህ የሕግ ማዕቀፍ ተካተዋል ወይ? ካልተካተቱ እንዲካተቱ ቢደረግ፤<br>- ከሴክዩሪቲ አንፃር እንዴት ታይቷል?<br>- ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ተያያዘ ማዕከሉ በሚኒስቴሩ ሆኖ ከክልሎች ጋር የተሳሰረ ሲስተም መዘርጋት አስፈላጊ ነው | ካሁን በፊት የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች እንደ አዲስ ምዝገባ በማድረግ አዲስ ሠሌዳ እንደሚሰጣቸው ተብራርቷል፤ ሴክዩሪቲን በተመለከተ ከደኅንነት አኳያ ታይቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሲፈቀድ ብቻ ተጨማሪ ሠሌዳዎች ሊሰጡ እንደሚችሉ፤ እንዲሁም የሠሌዳ እና የተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንደሚሆን በመመሪያው ተመላክቷል፡፡ | |

## 6. የረቂቅ መመሪያው ይዘት

ረቂቅ መመሪያው መግቢያ ያለው ሲሆን በሦስት ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡ በክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ማለትም፡- አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ የመመሪያው ዓላማዎች እና የተፈጻሚነት ወሰን ተካተዋል፡፡ በክፍል ሁለት ስለ ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አሰጣጥ መላትም፡-ስለ ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶች እና ምልክቶች፣ ስለ ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አሰጣጥ፣ የተስከርካሪ አምራች፣ ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት እና ግለሰብ ግዴታዎች፣ የተሽከርካሪ መዝጋቢ አካላት ግዴታዎች፣ የተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ ሠሌዳ ለመውሰድ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ይዟል፡፡ በክፍል ሦስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ማለትም፡-ክልከላዎች፣ አስተዳደራዊ እርምጃዎች፣ የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት፣ የአገልግሎት ክፍያ፣ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፣ ስለመረጃ አያያዝ ሥርዓት፣ የተሻሩ ሕጎች፣ መመሪያውን ስለማሻሻ እና መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ የሚሉትን ርዕሰ ጉዳዮች አካተ ይዟል፡፡

## 7. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የተሽከርካሪ ምዝገባ ሥርዓቱን በማዘመን የትራፊክ ቁጥጥሩን ለማጠናከር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመፍጠርና የሀብት አጠቃቀም ላይ የሚታየውን ብክነት በማስቀረት ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት ያደረገ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነትና ምልክቶች እና ሌሎች ምሥጢራዊ ምልክቶችን በማካተት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የአሠራር እንዲኖር በማድረግ የሠሌዳ አመራረት፣ አሰረጫጨት እና አወጋገድ፤ እንዲሁም የተሽከርካሪ ምዝገባን እንደ አዲስ በማካሄድ የተሽከርካሪ መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በታገዘ አግባብ ለመያዝና ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ለሀገር ዕድገት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

በሌላ በኩል ማንኛውም ተሽከርካሪ የየዕለት እንቅስቃሴው ምን እንደሚመስል እና የት ቦታ እንዳለ ጭምር ለመቆጣጠር የሚያስችል ሶፍት ዌር በማበልጸግ በሥራ ላይ እንደሚውል የተመላከተ ሲሆን በዚህ ቴክኖሎጂ በመታገዝ በየጊዜው በተሽከርካሪ

አማካይነት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መረጃ ጭምር ለማወቅና በቀላሉ ለሚመለከተው የፍትሕ አቅርቦ ተጠያቂ ለማድረግም የሚኖረው ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡